Arlington Public Schools

# የተማሪ ድጋፍ ሰጪ ቡድን (SST) ስብሰባ: የቤተሰብ/የአሳዳጊ አጠቃላይ እይታ

የተማሪ ስም፡-                                                    ቀን፡-

### የተማሪ ድጋፍ ቡድን ሰጪ *(SST)* ምንድነው *?*

SST በትምህርት ቤት ውስጥ ስለ አንድ ተማሪ አካዴሚያዊ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ፣ ባህሪ እና/ወይም የመላመድ ፍላጎቶች ዙርያ ሪፈራል ግምት ውስጥ ለማስገባት የሚሰበሰብ የትብብር እና ሁለገብ ቡድን ነው።

### የSST አባላት እነማን ናቸው*?*

እንደ ወላጅ/አሳዳጊ፣ ከአጠቃላይ ትምህርት መምህር፣ የልዩ ትምህርት መምህር፣ አስተዳዳሪ (ብዙውን ጊዜ "LEA" እየተባለ የሚጠራው - የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ ተወካይ)፣ የትምህርት ቤት የስነ ልቦና ባለሙያ፣ የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ እና ሌሎች በትምህርት ቤት እና/ወይም በቤተሰብ የተጋበዙ የቡድኑ አባላት **እኩል** የአባልነት ድርሻ አልዎት። በስብሰባው ላይ እንዲገኝ የምትፈልጉትን ሁሉ መጋበዝ ትችላላችሁ።

### በምን ጉዳይ ላይ ውይይት ይደረጋል?

- ተማሪውን የላከው (ሪፈር ያደረገው) ሰው (ወላጅ/አሳዳጊ ሊሆን ይችላል) ስጋቶችን ያጋራል።
- ስለልጅዎ ጠቃሚ መረጃ ይገመገማል።
- የሚገኝ ማንኛውም የህክምና መረጃ ግምት ውስጥ ይገባል።
- የወላጆች አስተያየት እና አመለካከቶች ይበረታታሉ እናም ታሳቢ ይደረጋሉ።

### የሚወሰነውስ ምንድን ነው*??*

ቡድኑ የሚከተሉትን ሊመክር ይችላል፡-

- የጣልቃገብነት እቅድ (በAPS የተማሪ ድጋፍ መመሪያ ውስጥ ስለ ጣልቃገብነት እቅዶች የበለጠ ማንበብ ይችላሉ) መንደፍ
- በክፍል 504 መሰረት ብቁ መሆንን ግምት ውስጥ ማስገባት
- ለልዩ ትምህርት ግምገማ ሪፈራል

ቡድኑ ግምገማ እንዲደረግ ከመከረ፣ እርስዎ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- ተስማምተው ፍቃድዎትን መስጠት። ልጅዎ ብቁ በሆኑ የትምህርት ቤት ባለሙያዎች ይገመገማል። ግምገማው በልጅዎ የተጠረጠሩት አካል ጉዳተኝነት ጋር የተያያዙ ሁሉንም ዘርፎች ይመለከታል። ይህ በልጅዎ ፍላጎቶች ላይ በመመስረት ጤናን፣ እይታን፣ መስማትን፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገትን፣ የአስተሳሰብ እና የመማር ችሎታን፣ የትምህርት ቤት ውጤትን፣ ተግባቦትን፣ እንቅስቃሴን እና የእለት ተእለት ኑሮ ችሎታዎችን ሊያካትት ይችላል። አንዳንድ የግምገማው ክፍሎች ማህበረሰባዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ትምህርታዊ፣ የመምህራን ምልከታዎች እና ሌሎች እንደ ንግግር/ቋንቋ ወይም የኦኪፔሽናል ቴራፒ (አስፈላጊ ከሆኑ) ግምገማዎች ሊያካትቱ ይችላሉ።
- አለመስማማት እና ፍቃድ አለመስጠት። የልዩ ትምህርት ግምገማ አይካሄድም።

### እንደ ወላጅ/አሳዳጊ የኔ ድርሻ ምንድነው?

- የSST እኩል አባል መሆንዎትን ያስታውሱ። የእርስዎ አመለካከት ዋጋ ያለው እና አስፈላጊ ነው።
- በስብሰባው ወቅት ውይይቱ ላይ ንቁ ተሳትፎ ያድርጉ። ማስታወሻ: ለመሳተፍ የቋንቋ ትርጉም እና/ወይም የADA መስተንግዶ ከፈለጉ ትምህርት ቤቱን ያሳውቁ።
- ሃሳቦችዎን፣ አመለካከቶችዎን እና የሚኖሮዎትን ማንኛውንም ስጋት ለማካፈል አያመንቱ።
- እንደየ አስፈላጊነቱ ጥያቄዎችን እና ማብራሪያ ይጠይቁ።
- ቡድኑ በልዩ ትምህርት ግምገማ ለመቀጠል ከወሰነ፣ ፈቃድዎን ለመስጠት ይፈልጉ እንደሆነ ያስቡበት።

# የተማሪ ድጋፍ ሰጪ ቡድን (SST) ስብሰባ: የቤተሰብ/የአሳዳጊ አጠቃላይ እይታ

## ለተማሪ ድጋፍ ሰጪ ቡድን ስብሰባ መዘጋጀት

የበለጠ ዝግጁነት እና በራስ የመተማመን ስሜት እንዲሰማዎት የሚከተሉት ነገሮችን ማድረግ ይችላሉ፦



- ☑ የልጅዎ ጠንካራ ጎኖች እና ተጨማሪ ድጋፍ ሊያስፈልጉት የሚችሉ መስኮችን ይለዩ።
- ☑ ከልጅዎ ጋር በመነጋገር ስለ ትምህርት ቤት ምን እንደሚሰማቸው እና በተሻለ ሁኔታ እንዲማሩ የሚረዳቸው ምን እንደሆነ ይጠይቁ።
- ☑ የትምህርት ቤቱ ቡድን ማሳየት የሚፈልጉትን ያልዎት የግል ግምገማዎች ወይም ሪፖርቶች ይሰብስቡ።
- ☑ ለቤተሰብዎ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ነገር እና በዚህ ስብሰባ ላይ ማሳካት የሚፈልጉዋቸውን ግቦች ለማወቅ ጊዜ ወስደው ያስቡበት። ሃሳብዎትን ለማደራጀት ከታች 'የመነጋገሪያ ነጥቦች' የሚለውን ክፍል መጠቀም ይችላሉ።

- ☑ በስብሰባው ወቅት መጠየቅ የሚፈልጉትን ጥያቄዎች ከታች "ጥያቄዎች" የሚለው ክፍል ላይ ይጻፉት።
- ☑ ስለ ልዩ ትምህርት የበለጠ ለማወቅ የወላጅ የመረጃ ማእከልን (PRC) ያግኙ። ከተቻለ፣ "የልዩ ትምህርት መግቢያ" ክፍለ ጊዜያቸውን ለመከታተል ይሞክሩ ወይም አሁን በመስመር ላይ ይመልከቱት! ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት ጥሩ መንገድ ነው።

- ☑ አንድን ሰው (እንደ ጓደኛ፣ ጠበቃ ወይም የቤተሰብ አባል) ከእርስዎ ጋር ወደ ስብሰባው ለማምጣት ካሰቡ ቦታ እና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት እንዲችል ትምህርት ቤትዎ አስቀድመው ያሳውቁ።

የPRC የመስመር ላይ ቪድዮ ሞጁሎች

WATCH NOW

| ሊታሰብባቸው የሚገባ ጥያቄዎች | የመነጋገሪያ ነጥቦች/ተጨማሪ ጥያቄዎች |
|---|---|
| • ለልጄ የሚቀጥሉት እርምጃዎች ምንድን ናቸው እና ልጄን ለቀጣይ እርምጃዎች ለማዘጋጀት ማድረግ ያለብኝ ነገር አለ?<br>• ከስብሰባው በኋላ ላካፍላቸው የምፈልገውን ጥያቄዎች ወይም መረጃዎች ካሉ ከሌሎች በተሻለ መልኩ የትኛው የቡድኑ አባል ማግኘት አለብኝ?<br>• ልጄን በቤት ውስጥ የበለጠ እንዴት መርዳት እችላለሁ?<br>• SST የጣልቃ ገብነት እቅድ ለመፍጠር ከወሰነ፣ የጣልቃ ገብነት እቅዱ የተሳካ መሆኑን እንድናውቅ የሚረዳን ግብረመልስ መቼ እና እንዴት ከኛ ጋር ይጋራል?<br>• SST የልዩ ትምህርት ግምገማ እንዲደረግ ከወሰነ፦<br>  ◦ ልጄ መቼ ነው የሚገመገመው?<br>  ◦ የትኞቹ ምዘናዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ እና እንዴት ይወሰናሉ?<br>  ◦ የብቃት ስብሰባ ከመደረጉ በፊት መመርመር እንድችል የግምገማ ክፍሎቹ መቼ እና እንዴት ማግኘት እችላለሁ?<br>  ◦ የስነ-ልቦና ግምገማ ከተጠናቀቀ፣ ከስብሰባው በፊት ግኝቶችን ከስነ አእምሮ ባለሙያ ጋር ለመወያየት እድሉ ይኖረኛል?<br>• SST የክፍል 504 ግምት ውስጥ እንዲገባ ሐሳብ ከሰጠ፣ ለክፍል 504 የኮሚቴ ስብሰባ እንዴት መዘጋጀት አለብኝ? | |

LEARN MORE

እርስዎ ለመርዳት PRC እዚህ ይገኛል። 703.228.7239 ላይ ይደውሉሉን ወይም prc@apsva.us ኢሜል ይላኩልን።

PEATC:- ጠቃሚ የወላጅ መብቶች

የAPS ተማሪ ድጋፍ መመሪያ

የAPS ክፍል 504 መረጃ

PEATC:- ምዘናዎችን መረዳት

PEATC: ለብቁነት ሪፈራል

የVDOE የሪፈራል ቪድዮ